# <u>የእፅዋት አለም</u>

ሁላችሁም ኑ! እንሂድ!

የት?

ኑ!... ወደ እፅዋት አለም፡፡

እዚህ ጋር እንዴት ያምራል...

በሚሊዮን የሚቆጠሩ እፅዋት እዚህ ይኖራሉ፡፡

ደማቅ ከለር ያላቸው እና በጣም ንፁህ የሆኑ አበቦች...

ሁሉም የፍራፍሬ አይነቶች...

አትክልቶች...

ዛፎች...

እንዴት ያምራሉ!

አሁን ስለዚህ አለም አባላት ቀረብ ብለን እንመልከት፡፡ እንዴት እንደሚራቡ እንማር፡፡ እንደዚሁም ለመራባት የሚጠቀሙበትን ዘዴ እንይ፡፡

ሁላችሁም ትላልቅ ዛፎች እነኳን ከትንሽ ፍሬ እንደሚበቅሉ ታውቃላችሁ፡፡እነዚህ ፍሬዎችስ ከየት እንደመጡ ታውቃላችሁ?

*የሱፍ አበባ፡ እኔም እንዲሁ ትንሽ ዘር ነበርኩ፡፡ እንዴት እንደተፈጠርኩ የማወቅ ከፍተኛ ጉጉት አለኝ፡፡*

ዘር እንዲፈጠር በእፅዋቱ ውስጥ የሚገኘው የሴቴ ሴል ከሌላኛው አፅዋት የወንዴ የእርባታ ሴል በሌላ አገላለፅ ከወንዴ የአበባ ዱቄት ጋር መገናኘት አለበት፡፡

የሱፍ ደበባ፡ እፅዋቶች አይንቀሳቀሱም፡፡ ግን ይህን እንዴት ማድረግ ይችላሉ?

ትክክል ነሽ እፅዋቶች አይንቀሳቀሱም ነገር ግን አላህ (ሱ.ወ) የአንደኛው አበባ የአበባ ዱቄት ከሌላኛው ጋር የሚገናኙባቸው ብዙ መንግዶችን ፈጥሯል።

አብዛኛው የአበባ ዱቄት በንፋስ አማካኝንት ይጓዛል።

አንዳንድ ሰዎች ይህን አይወዱትም። ምክንያቱም እነዚህ ጥቃቅን ቅንጣቶች በፀደይ ወራት ብዙ ሰዎች ላይ ለሚፈጠረው አላርጂክ መንስኤ ስለሆኑ ነው።

*የሱፍ አበባ፡ አቲሾ! በፀደይ ጊዜ ያስለኛል...*

የአበባ ዱቄት ወደ ዘርነት መለወጥ የሚጀምረው የሴቷን እንቁላል የያዘ ሌላ የአበባ ዱቄት ጋር ሲደርስ ነው።

አንዳንድ እፅዋቶች የአበባ ዱቄታቸውን ወደ ሌሎች እፅዋት ለመላክ ልዩ የሆኑ ተሸካሚዎችን ይጠቀማሉ።

ከእነዚህ በጣም የተለመዱት ነፍሳቶች ናቸው።

አበቦች ነፍሳቶች የሚወዷቸውን ምግቦች በማምረት በደማቅ ከለራቸው እና በሽቶዋቸው ይስቧቸዋል። በዚህም ምክንያት የአበባ ዱቄታቸውን በእነሱ አማካኝነት ከቦታ ቦታ ማዘዋወር ይችላሉ ። ነፍሳቶችም እነዚህን የአበባ ዱቄቶች ወደ ሌሎች እፅዋቶች ያጓጉዛሉ።

በእነዚህ የተለያዩ ፍጥረታት መካከል ያለው ሰላማዊ ግንኙነት ግልፅ የሚሆንልን በአበቦች እና በነፍሳት መካከል ያለውን ግንኙነት በደንብ ስናጤን ነው።

የዚህ አንዱ ምሳሌ ይህን ይመስላል...

ይህ በደቡብ አፍሪካ የሚበቅል አበባ ሲሆን አይሪስ በመባል ይታወቃል።

የአበባ ዱቄት ለሚሸከሙ ነፍሳቶች በዚህ ማራኪ አበባ የተሰሩትን ምግቦች እና የአበባ ዱቄቱን መድረስ እጅግ አስቸጋሪ ነው።

ተመልከቱ! ከቅጠሉ በታች ረዥም ትቦ ይገኛል።

ምግቡ እና የአበባ ዱቄቱ በዚህ ትቦ ታችኛው ክፍል ውስጥ ይገኛሉ።

የአበባ ዱቄቱን የሚሸከመው ነፍሳትም እነሱን ለመድረስ ረጅም ትቦ ያስፈልገዋል፡፡

*የሱፍ አበባ፡ ይህ ማለት እኛ ከረጅም ጠርሙስ ለመጠጣት የመጠጫ ቀሰምን እንደምንጠቀምው አይነት ስርዓት ነው የሚያስፈልገው፡፡*

የዚህ እፅዋትን የአበባ ዱቄትም የሚደርስ ነፍሳትም ይገኛል፡፡ ይህም ሁቨር ፍላይ ይባላል፡፡

ለረጅሙ ትቦ ወይም ‘ፕሮቦሲስ’ ምስጋና ይግባው የአበባውን ውስጣዊ ክፍል መድረስ ይችላል፡፡ እንዲሁም ልክ እንደሂሊኮፕተር አየር ላይ ማንዣበብ ይችላል፡፡

ሂሊኮፕተር ደህንነቱ ተጠብቶ እንዲያርፍ ልዩ የሆኑ ምልክቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

ሁቨር ፍላዮ ተመሳሳይ ምልክትን ይጠቀም ይሆን ብላችሁ ልትጠይቁ ትችላላችሁ?

በአበባው ላይ የሚገኙትን ነጫጭ ቀስቶች በደንብ እንመልከት፡፡

ሁሉም ወደ አንድ አቅጣጫ በማመልከት ሑቨር ፍላዮ የቱጋር ማረፍ እንዳለበት ይጠቁሙታል፡፡

ሁቨር ፍላዮም በትክክለኛው ቦታ ላይ በውጤታማነት ማረፍ ይችላል፡፡

አሁን ስለተመለከትናቸው ነገሮች እናስብ፡፡ አበባ የማያስብ የሆነ የማያስብ እፅዋት ክፍል ነው፡፡ አይን፣ ጆሮ፣ እጅ ወይም የሚያስብበት አእምሮ የለውም ሆኖም ነፍሳቱን የቱ ጋር ማረፍ እንዳለበት የሚያመላክት ምልክት አለው፡፡ አበባው እራሱ ይህን ስለመያዙ አይረዳም፡፡

ነፍሳቱም ልክ እንደ አበባው ሕሊናም ሆነ የማሰብ ችሎታ የለውም፡፡ ነገር ግን የአበባ ዱቄቱን ለመድረስ የሚያስፈልገው ልዩ የሆኑ ገፅታዎችን በሙሉ ይዟል፡፡

አላህ ነው አበባውን እና ነፍሳቱን እንዲስማሙ አድርጎ የፈጠራቸው፡፡ አላህ እያንዳንዱን ፍጥረት ምን አይነት ባህሪይ እንደሚያስፈልገው ያውቃል፡፡ እናም ተስማሚ ባህሪያትን ይለግሰዋል፡፡ በቅዱስ ቁርአን ላይ አላህ የሚከተውን ብሏል፡፡

“በሰማያት እና በምድር ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው፡፡ ሁሉም ለርሱ ተዛዦች ናቸው፡፡” (ሱርቱ ሩም፡ 26)

## ሽቶን የሚሠጡ አበቦች

የተወሰኑ አበቦች ነፍሳትን ለመሳብ አስደናቂ ዘዴን ይጠቀማሉ፡፡

ሽቶ ይጋብዟቸዋል፡፡

ይህ በደቡብ አሜሪካን ውስጥ የሚገኝ ኦርኬድ በቅጠሎቹ ላይ ልዩ የሆነ ሽቶን ያዘጋጃል፡፡

የዚህ ሽቶ ደንበኞች ወንድ ንቦች ናቸው፡፡

*የሱፍ አበባ፡ የሰው ልጆችም መልካም መዐዛ ይኖራቸው ዘንድ ሽቶን ይጠቀማሉ፡፡ ኡህ!... ሽታው በጣም ደስ ይላል፡፡*

ንቦችም ልክ እንደ ሰዎች መልካም መዐዛ እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ፡፡

ንቡ ከኦርኬዱ ሽቶን ለመውሰድ ሲመጣ አበባውም ኀበኚውን የአበባ ዱቄት ይሰጠዋል፡፡ እንዴት? እስቲ እንመልከት!

ሽቶ የሚገኝበት ቦታ መግቢያ በጣም ያንሸራትታል፡፡ አ! አ! አ!

ንቡ እራሱን ለማስለቀቅ ሲታገል ከቢጫው የአበባ ዱቄት ጋር ይነካካል፡፡

የአበባ ዱቄቱም ከሰውነቱ ጋር ይጣበቃል፡፡

አዝርእት የአበባ ዱቄቱ የሴቴ ክፍል ከደረሰ በኋላ ይፈጠራሉ፡፡

ጓደኞቹ ዘሩ እፅዋቱ ተተኪ ትውልድ እንዲኖረው ይረዳል፡፡ እያንዳንዱ ዘር የአላህ የመፍጠር ጥበብ ምሳሌ ነው፡፡

ሁሉንም ነገሮች የፈጠረው ሀያሉ አላህ ስለ ዘር አፈጣጠር በቁርአን ላይ እንደሚከተለው ይገልፃል፡፡

**"የምትዘሩትንም አያችሁን? የምታበቅሉት እናንተ ናችሁ ወይስ እኛ ነን አብቃዮቹ? ብንሻ ኖሮ ደረቅ የተሰባበረ ባደረግነው እና በተከፋችሁም ነበር፡፡" (ሱረቱል ዋቂአ:63-65)**

## የሚበሩ አዝርዕት

አሁን የምትመለከቷቸው አዝርዕት አየር ላይ ላይ በመብርር ይሠራጫሉ፡፡

በእያንዳንዱ ነጭ ኳስ መሳይ ነገር ላይ በመቶዎች የማቆጠሩ አዝርእት ይገኛሉ፡፡

እነዚህ አዝርእት ለመብረር የሚያስችላቸው ልዩ የሆነ ስርዓት አላቸው፡፡

*የሱፍ አበባ፡ ተመልከቱ! ሲበሩ እንዴት ደስ እንደሚሉ ልክ ፓራሹት ያላቸው እኮ ነው የሚመስሉት…*

ይህ ፓራሹት ምሉእ በመሆኑ በትንሽ ትንፋሽ እንኳን አዝርእቱ አየር ላይ ሊንሳፈፉ ይችላሉ፡፡

እነዚህ የምትመለከቷቸው እያንዳንዳቸው ትናንሽ ሂሊኮፕተሮች አንድ ዘር ይዘዋል፡፡ የዘሩ መጠን ከክንፉ ቅርፅ እና ርዝመት ጋር የተመጣጠነ ነው፡፡ ይህ ስርዓትም ልክ እንደ ፓራሹት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

ፓራሹትን የሚሠሩት ማሰብ የሚችሉ እና የተማሩ ሰዎች ናቸው፡፡

ነገር ግን እነዚህ አዝርእት በሰዎች ከተሰሩት ፓራሹቶች እጅግ በበለጠ ውጤታማ የሆኑ ፓራሹቶችን ይጠቀማሉ፡፡ ሆኖም እነሱ ማሰብ የማይችሉ እፅዋት ናቸው፡፡

ሕሊናም ሆነ የመመራመር አቅም የላቸውም፡፡ ነገር ግን ለአላህ አቻ የለሽ ፈጠራ ምስጋና ይግባው ለአዝእርቶቻቸው የሚያገለግሉ ምርጥ ፓራሹቶች አሏቸው፡፡

## ባለ ክንፍ አዝርእት

*የሱፍ አበባ፡ ኑ! ወደ አማዞን ደን እንሂድ፡፡ ኦ! እዚህ በጣም ይሞቃል እንዲሁም አየር በደንብ አይነፍስም፡፡ ለአዝርእት እዚህ መብረር ከባድ ነው፡፡*

እዎ በዚህ ሞቃት እና ነፋስ የለሽ አየር መብረር ለአዝርእት እጅግ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡

ለዚያ ነው ዛፎች ዘሮቻቸውን ለማሰራጨት ምሉዕ የሆኑ ክንፎችን የሚጠቀሙት፡፡

የዛፉ ዘር ከምትመለከቱት ክንፍ ስር ይገኛል፡፡

እነዚህ ክንፎች በትንሽ የንፋስ እንቅስቃሴ ብቻ አዝርዕትን ረጅም ርቀት ይዘዋቸው ይሄዳሉ፡፡ ስለዚህ ዘሩ ከነበረበት ዛፍ በመራቅ ረጅም ርቀት ይሄዳል፡፡

## ሂሊኮፕተሮችን የሚጠቀሙ እፅዋት

ጥቂት ዛፎች አዝርዕቶቻቸው እንዲበሩ ሂሊኮፕተሮችን ይጠቀማሉ፡፡

*የሱፍ አበባ፡፡ ተመልከቱ! ተመልከቱ! ለክንፎቹ ምስጋና ይግባቸው፡፡ አዝርእቶች አየር ላይ እየተንሳፈፉ ነው፡፡*

ይህ ቅጠል ትንሽ ያነሰ ቢሆን ኖሮ ዘሩ መሬት ላይ ይወድቅ ነበር፡፡ ነገር ግን ተገቢ የሆነ መጠን ነው ያለው፡፡

እንዲሁም የዘሩ ክብደትም ከቅጠሉ ጋር የተመጣጠነ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሚጠቀመው ስርአት የሰው ልጆች ከሚጠቀሙት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ አሜሪካዊው የአውሮኘለን ዲዛይነር ኢጎር ሴኮርስኪ የመጀመሪያውን ሂሊኮኘተር በነዚህ አዝርእቶች እና በበረራ ስርዓታቸው በመማረክ ሰራ፡፡

ለቅጠሎቹ ምስጋና ይግባቸው ዘሩ ረጅም ርቀቶችን ይጓዛል፡፡

ይህም ማለት ዛፉ ትውልድ ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

ግንድ እና ቅጠል የሆነው አእምሮም ሆነ የማሰብ ችሎታ የሌለው ዛፍ እንዲህ አይነት ምሉእ የሆኑ ክንፎችን መስራቱ የማይሆን ነው፡፡

*የሱፍ አበባ፡ እነዚህ ባህሪያት በድንገት ሊገኙ ይችላሉን?*

ይህን የመሰሉ ምርጥ ገፅታዎች በድንገት ነው የመጡት ማለት የእብደት የመጨረሻ ገፅታው ነው፡፡

አላህ እነዚህን ዛፎች፣ አዝርእታቸውን እና የሚሸከሟቸውን አውሮኘላኖች እንደፈጠራቸው አያጠራጥርም፡፡

በአንድ የቁርአን አንቀፅ አላህ እንዲህ ይላል፡፡

“ጌታችሁ ያ ከርሱ ሌላ አምላክ የሌለ እውቀቱም ሁሉንም ነገር ያዳረሰው አላህ ነው፡፡” (ሱረቱል ጠሀ፡98)

## ዘራቸውን የሚተኩሱ እፅዋት

አንዳንድ እፅዋት አዝርእታቸውን ለማሠራጨት አስደናቂ ዘዴን ይጠቀማሉ፡፡

ወደአየር ይተኩሷቸዋል፡፡

ይህ የዱባ ፍንጣቂ ነው፡፡

በአላህ (ሱ.ወ) ለተፈጠረው ልዩ ስርዓት ምስጋና ይግባው አዝርእቱ በከፍተኛ ግፊት ውስጥ ይቆያል፡፡

*የሱፍ አበባ፡ እና ጊዜያቸው ሲደርስ ቡም!*

ይህ የሄሚሊያን በልሰም ነው፡፡

ይህ ስርዓት እጅግ ፍፁም በመሆኑ ከአካሉ ጋር የሚደረግ ትንሽ መነካካት የተኩስ ሂደቱን ያስጀምራል፡፡

የሚጫነው ሀይል ከፍተኛ ነው በዚህም ምክንያት እፅዋቱ እዝርእቱን እስከ አምስት ሜትር ወይም አስራ ስድስት ጫማ ማፈናጠር ይችላል፡፡

## ጀልባን የሚጠቀሙ እፅዋት

ጓደኞቼ አንዳንድ እፅዋት አዝርእታቸውን ለማሰራጨት አየርን ብቻ ሣይሆን ውሀንም ይጠቀማሉ፡፡ በዚህም ምክንያት አዝርዕቶቻቸው በውሀ ላይ መጓዝ ይችላሉ፡

ይህ የባህር ባቄላ ነው፡፡

አዝርእቶቹ የአለማችን ምርጥ የባህር ተጓዦች ናቸው፡፡

*የሱፍ አበባ፡ ጓደኞቼ! በውሀ ላይ መጓዝ ቀላል ነገር አይደለም…*

እያንዳንዱ ዘር የራሱ የሆነ የተለየ ሽፋን አለው።

ስለዚህ በመነጣጠል በተለያየ አቅጣጫ መጓዝ ይችላሉ።

ተመልከቱ! የወንዙ ፍሰት ወደ ባህሩ እየወሰደው ነው።

ከብዙ ኪ.ሜትር ጉዞ በኋላ ወደ ባህር ይደርሳል።

ሽፋኑ ዘሩን እንዳይበላሽ ከመጠበቁ በተጨማሪ እንደ መንሳፈፊያነት ያገለግላል።

ይህ በባህር ላይ የሚካሄደው ጉዞ ወራትን ወይም አመታትን ይፈጃል።

ምንም እነኳን የባህር ላይ ጉዞው አስቸጋሪ ቢሆንም ዘሩ በሕይወት ይቆያል።

የላይኛው ሽፋን ከተባለሸ የዘሩ ጠንካራ ሽፋን ዘሩን ይጠብቀዋል።

በስተመጨረሻም ሕይወቱን የሚቀጥልበት ደረቅ መሬት ላይ ይደርሳል።

አዲስ የባህር ባቄላ ዛፍ ከተገኘበት ዛፍ በሺዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን ርቆ ስሮቹን መትከል ይጀምራል።

## ከጉንዳኖች ጋር የሚኅዳኙ እፅዋት

*የሱፍ አበባ፡ የአለማችን ታታሪ የነፍሳት ዝርያዎች እነማን እንደሆኑ ታውቃላችሁ? ጉንዳኖች ናቸው...*

ጉንዳኖች ከሌሎች ነፍሳቶች በተሻለ ትጉህ እና ጠንካራ ሠራተኛ ናቸው።

እፅዋቶች የጉንዳኖችን ምርታማነት በመጠቀም አዝርእታቸውን እንዲሸከሙ ያደርጓቸዋል።

በዚህም ልውጫ ለጉንዳኖች ልዩ ሽልማትን ይሠጧቸዋል።

አዝርእታቸው በጉንዳኖች ለምግብነት የሚውል ደንዳና ሽፋን አላቸው።

አዝርእቱ ክፍት ቢተዉ በወፎች ወይም በሌሎች ፍጥረታት ይበላሉ።

መቆየት እና ማደግ ካለባቸው መሬት ውስጥ ቶሎ መግባት ይኖርባቸዋል።

## *የሱፍ አበባ፡ ጉንዳኖች ስራ ላይ ናቸው!*

ጉንዳኖች አዝርእታቸውን ወደ መሬት ውስጥ እያስገቡ ነው።

በአዝርእቱ ላይ ያለውን የፋፋ ምግብ በመመገብ ዘሩን ይተውታል።

ስለዚህ ዘሩ በደህንነት የሚያድግበት መሬት ውስጥ ይገባል።

የፍራፍሬ ዘሮች ተመሳሳይ ዘዴን ይጠቀማሉ።

እንሰሳት እና የሰው ልጆች አዝርእታቸውን እንዲሸከሙ ያደርጋሉ።

ዘሩ ሲበስል ደንዳናው የፍሬው ለስላሳ ክፍል ከለሩን በመቀየር ጣፋጭ ይሆናል።

እንሰሳት እና የሰው ልጆች እንዲቀጥፉት ይጋብዛል።

ወፎች የነዚህ ፍራፍሬዎችን ማራኪነት መቋቋም አይችሉም። ስለዚህ አበዛኛዎቹን ይመገቧቸዋል።

## *የሱፍ አበባ፡ አሁን በድጋሚ እናስተንትን!*

እፅዋቶች ጣፋጭ ፍራፍሬዎችን ለኛ ለማምረት አፈርን፣ ውሀን የፀሀይ ብርሀንን ይጠቀማሉ።

የሰው ልጆች እና እንሰሳቶች የሚያስፈልጋቸውን ያውቁ ይመስል ጤናማ ምግቦችን ያመርታሉ።

ከዚህም በተጨማሪ እነዚህን ፍራፍሬዎች የሚያመርቱት የአዝርእታቸውን ስርጭት በሚያረጋግጥ መልኩ ነው።

ዛፎች ከእንጨት፣ ከስር እና ከቅጠላ ቅጠል መሠራታቸውን አትዘንጉ። የማሰብም ሆነ የማመዛዘን ችሎታ የላቸውም።

ነገር ግን ጠቃሚ እና ጣፋጭ ምግቦችን ለእኛ እና ለእንሰሳት ያመርታሉ።

አላህ ነው እኛን እና ሌሎች ፍጥረታትን የፈጠረው። እንዲሁም ዛፎችን በዚህ መንገድ ፍራፍሬዎችን እንዲያመርቱ ያስቻለው።

በአንድ የቁርአን አንቀፅ አላህ (ሱ.ወ) ይጠራናል፡፡

“እርሱ ከሰማይ ውሃን ያወረደው አምላክ ነው፡፡ በርሱም ሁሉንም አይነት እፅዋት አበቀልን፡፡ የተደራረበ ቅንጣት የምናወጣበትን ለምለም አዝመራ ከርሱ አወጣን፡፡ከዘንባባም ከእንቡጡ የተቀራረቡ የሆኑ ዘላላዎችን አወጣን፡፡ የወይን አትክልት ቦታዎችንም አዘጋጀን፡፡ ቅጠሎቻቸው የሚመሳሰሉ እና ፍሬዎቻቸው የማይመሳሰሉ የሆኑትን የዘይቱን እና የሩማን እፅዋትንም ከሰማይ ባወረድነው ዝናብ አበቀልን፡፡ የሰው ልጆች ሆይ!ፍሬውን ባፈራም በበሰለም ጊዜ ተመልከቱት፡፡ በነኚህ ክስተቶች ውስጥ ለሚያምኑ ሰዎች በርካታ ተአምራት አሉ፡፡” (ሱረቱል አንአም፡99)

<u>መደምደሚያ</u>

በዚህ ፊልም ላይ ብዙ ሰዎች ስላልተገነዘቧቸው የአዝርእት እና የአበባ ዱቄት ተአምራት ስንመለከት ነበር፡፡

ነፍሳቶችን የሚጠቁሙ አበቦች ….

ለነዚህ አበቦች በልዩ ሁኔታ የተፈጠሩ ነፍሳት…

ለንቦች ሽቶን የሚለግሱ ኦርኬዶች…

ልክ እንደመሀንዲሶች ፓራሹቶችን የሚጠቀሙ አዝርእት…

እንዲሁም በሺዎች የሚቆጠሩ ኪ.ሜትሮችን በባህር ላይ የሚጓዙ አዝርእት..

እፅዋት ሌሎች ፍጥረታት ዘሮቻቸውን እንዲሸከሙ የሚያደርጉበትን አስደሳች ዘዴ ተመልክተናል፡፡

እነዚህ በእፅዋት ውስጥ የሚገኙ ስርዓቶች እጅግ ምሉዕ እና በድንገት ሊገኙ የማይችሉ እንደሆኑ ተመልክተናል፡፡

ሁሉን አዋቂው ሐያሉ አላህ ነው እነዚህን በሙሉ የሚያንቀሳቅሰው፡፡ እሱ ነው ስለ ፍጥረታት እና ስለ እፅዋት ፍላጎት በማወቅ የተለያዩ ዘዴዎችን ለእነሱ አገልግሎት የሚያውለው፡፡

አላህ በዚህ ርእስ ላይ አትኩሮት ይሰጣል፡፡

**“አላህ ቅንጣትን እና የፍሬን አጥንት ፍልቃቂ ነው፡፡ ከሙት ሕያውን ያወጣል፡፡ ከህያውም ሙትን አውጭ ነው፡፡ አላህ ይህ ነው፡፡…” (ሱረቱል አንአም፡95)**